..MENT COMMISSION
ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት
ኮሚሽን

THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN INVESTMENT
COMMISSION

ቀን 22 ህዳር 2009
DATE

ቁጥር ኢጠ/22/30
REF. NO.

ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- የሀገር ውስጥ ባለሀብት የባለ ኮከብ ደረጃ ያላቸው የሆቴል ኢንቨስትመንት የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ አፈፃፀምን ይመለከታል

የባለ ኮከብ ደረጃ ላላቸው ሆቴሎች የኢንቨስትመንት ፈቃድ በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 4(1) (መ) መሰረት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኩል መሰጠት ሲገባው በስህተት በንግድ ሚኒስቴር በወጣው በኢትዮጵያ የንግድ መስጫ መደቦች የአማርኛው ክፍል የባለ ኮከብ ሆቴሎች የንግድ ስራ ፈቃድ ሰጪ የክልል የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ እንደሆነ በመገለጹ በክልሎች የኢንቨስትመንት ፈቃድ እየተሰጠ መቆየቱን ተረድተን ይህ ድርጊት እንዲቆም ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም. በቁጥር ኢ.ኢ.ኮ/አጠ120/9 ለሁሉም ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እና የከተማ አስተዳደር የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች የባለ ኮከብ ደረጃ ሆቴሎች ከታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም. ጀምሮ የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚሰጠው በአዋጁ መሰረት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በኩል መሰጠት የሚገባው መሆኑን አስታውቀን ነበር፡፡

ይሁን እንጂ ከኢንቨስትመንት ፈቃዱ አሰጣጡ ጋር ተያይዞ በክልሎች ሲሰጥ በቆየው የጉምሩክ ቀረጥ ነጻ ማበረታቻ አፈጻጸም ላይ ችግሮች እየተስተዋሉ መሆኑና ከኢንቨስትመንት አዋጁ ዓላማ ውጪ እየዋለ በመሆኑ፣ ይህም ሳይታረም በነበረው ሁኔታ ...ቀጥል ማድረጉ አግባብ ባለመሆኑ፡-

1ኛ/ ከታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም. በኋላ የባለ ኮከብ ደረጃ ላላቸው ሆቴሎች በክልሎች እና በከተማ አስተዳደሮች የተሰጠ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ቢኖር ህጋዊ ባለመሆኑ ምንም ዓይነት የቀረጥ ነጻ ማበረታቻ አገልግሎት እንዳያገኝ እንዲደረግ፣

2ኛ/ ታህሳስ 22 ቀን 2008 ዓ.ም. በፊት በክልሎች የተሰጡ የባለ ኮከብ ሆቴሎች የኢንቨስትመንት ፈቃዶች ግን በአሁኑ ጊዜ በአግባቡ ወደ ሥራ የገቡትን ለይተን ዝርዝራቸውን እስከምናሳውቃችሁ ድረስ በዚህ ወቅት በክልሎች በተሰጠ

የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚጠየቅ ማንኛውም አይነት አገልግሎት ቢኖር እንዲቋረጥ፣

ስለዚህ ከላይ በተገለጸው መሰረት በተገልጋዮች ላይ ቅሬታ ሳይፈጠር እና መመሪያውም ሳይጣስ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል አፈጻጸሙን ሁሉም ክልሎች አውቀውት ለተግባራዊነቱ የበኩላቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ ለሁሉም በዚህ ደብዳቤ ግልባጭ እንዲያውት ተደርጓል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ም አረጋ
ሚሽነር

<u>ግልባጭ</u>:-

- ለሁሉም ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እና የከተማ አስተዳደር
  የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ መ/ቤቶች
  <u>በያሉበት፣</u>
- ለኢፌዴሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር
  <u>አዲስ አበባ፣</u>
- ለምክትል ኮሚሽነሮች
- ለሁሉም ዳሬክቶሬቶች
  <u>ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን</u>